ሜትሮፖሊታን ፖሊስ ዲፓርትመንት
ፒተር ኒውሻም
የፖሊስ ቺፍ

የኮሚኒኬሽንስ ቢሮ
ደስቲን ስተርንቤክ
ዳይሬክተር

# ዜናዎች

ባፋጣኝ ይለቀቅ

*የህዝብ መረጃ ቢሮ፡* 202- 727-4383

ማርች 26፣ 2020

## ኤም.ፒ.ዲ. በዋሺንግተን ዲ.ሲ. ስለ ከኮሮናቫይረስ ጋር የተያያዙ ማጭበርበሮች ያስጠነቅቃል

(ዋሺንግተን ዲ.ሲ.) - ሜትሮፖሊታን ፖሊስ ዲፓርትመንት (ኤም.ፒ.ዲ.) በዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ ከኮሮናቫይረስ (ኮቪድ-19) ጋር የተያያዘ ሊከሰት ስለሚችል የማጭበርበር ድርጊት ለህብረተሰቡ ማስጠንቀቅ ይፈልጋል።

በዚህ የማህበረሰብ ጤና አስቸኳይ ጊዜ አጭበርባሪዎች ዜጎችን በተለያዩ መንገዶች ለማጭበርበር እየሞከሩ ነው። ኤም.ፒ.ዲ. በቅርቡ በዲስትሪክቱ ወደየ በሩ እየሄዱ "የኮሮናቫይረስ ኢንሹራንስ" ለመሸጥ የሚሞክሩ ግለሰቦች እንዳሉ ጥቆማ ደርሶበታል። እነዚያ ግንኙነቶች የማጭበርበር ድርጊቶች ናቸው ተብለው ይጠረጠራሉ።

የማህበረሰቡ ደህንነት ለመጠበቅ በምናደርገው ጥረት ይረዳ ዘንድ ማህበረሰቡ የሚከተሉትን ከኮቪድ-19 ጋር የተያያዙ የማጭበርበር ስራዎች ይርቅ ዘንድ ኤም.ፒ.ዲ. ይጠይቃል፡

- ለኮቪ.ድ-19 እንደነ መድህኒት፣ ክትባት፣ እና ኢንሹራንስ የመሳሰሉ ህክምና እንሸጣለን ከሚሉ ግለሰቦች።
- ከፍተኛ ፍላጎት ያላቸው እንደነ የቀዶ ጥገና ጭምብሎች (ሰርጂካል ማስክስ) የመሳሰሉ አቅርቦቶች በኦንላይን ከሚደረጉ ሽያጮች።
- ለኮቪ.ድ-19 ህክምና እና ሌላ የህክምና አገልግሎቶች የሚውል ገንዘብ ከሚጠይቁ የቴሌፎን ጥሪዎች ወይም ኢመይሎች።
- በኮቪ.ድ-19 ለተጠቁ የሚውል ተብለው ከሚጠየቁ የድጋፍ ጥያቄዎች።
- ከብሔራዊና አለም አቀፍ የጤና ባለስልጣናት የግል እና/ወይም የፋይናንስ መረጃ ከሚጠይቁ የማስገር (ፊሺንግ) የቴሌፎን ጥሪዎች፣ የጽሁፍ መልእክቶች ወይም ኢመይሎች።
- ይፋዊ ያልሆነ፣ የተጠቃሚዎች መሳሪያዎችና የግል መረጃዎች በማልዌር (ተንኮል አዘል ሶፍትዌር) ሊወስዱ ከሚችሉ የኮቪ.ቭ-19 አፖች ወይም ዳውሎዶች።
- ኮቪ.ድ-19ኝን እንከላከላለን፣ እንለያለን (ዲተክት) ወይም እንፈውሳለን ከሚሉ ኢንቨስትመንቶች።

ዲፓርትመንቱ እንደነዚህ ለመሳሰሉ ጉዳዮች በጠና ይከታተላቸዋል፣ በእንደነዚህ እኩይ ስራዎች ለሚሳተፉ ወንጀለኞች ለሚያደርጉት ነገር ተጠያቂ ያደርጋቸዋል።

በዋሺንግተን ዲ.ሲ. የኮሮናቫይረስ ማጭበርበሮች ሰለባ ከሆኑ ወይም የማጭበርበር ስራ ነው ተብሎ ስለሚጠረጠር ነገር እውቀት ካለዎት እባክዎ የሜትሮፖሊታን ፖሊስ ዲፓርትመንት የገንዘብ እና የሳይበር ወንጀሎች ክፍል በስልክ ቁጥር 202-727-4159 ወይም በኢመይል mpd.fraud-unit@dc.govያግኙ።

ኮቪ.ድ-19 በተመለከተ ተጨማሪ መረጃና ጠቃሚ ሀብቶች ቢፈልጉ እባክዎ coronavirus.dc.gov ይጎብኙ።